# ከሰሞኑ ጫጫታ ባሻገር፣ የትብብሩ መሠረቶችና ተግዳሮቶች በቅጡ መዳሰስ

ዩሱፍ ያሲን (ኦስሎ)

**ከሰሞኑ ጫጫታ ባሻገር**

የሞላ አስገዶም ኮብለላ ፣ ፍርጠጣ ክሕደት ወይም በመንግሥት ደጋፊዎች እንደ ተባለው ወሸመጥ በጣሽ የጀግንነት ሥራ በአሥመራ ተጓዞችና ደርሶ–ተመላሾች መሓል እየተቋጠረ መጥቷል ብለን ያሰብነው ንትርኩን እንደገና አደበላለቀው። ቀድም ብሎ በስምምነት ባይደመደምም ቅሉ እልባት እተበጀለት የመጣ ሲመስል የነበረው ትግል በአሥመራ በኩል ያዋጣል፣ አያዋጣም ባዮች መሓል በትግል ምርጫና በትግል ማንኮባኮቢያ መሬት፣ የአስተናጋጁ መንግሥት ቃልኪዳን ጠባቂነትና ቃል አባይነቱ ዙሪያ በተለያዩ የኢትዮጵያ ታቃዋሚ ኃይሎችና ጉዳዩ ይመለከተናል ባይ ግለሰቦች መሓል ጊዜ ያስቆጠረው ንትርክና እሰጣ አገባን እንደ አዲስ አቀጣጠለውና ሰሞነኛው የወይይት ርእሰ ጉዳይ አድርጎት አረፈው የሞላ ኮብለላ ። ጥሬ አረገው ባይባልም ቅሉ እንደገና ትኩስ አረገው። ላለፉት ሦስት ሳምንታት እያንጫጫን የሚገኘው የሞላ ጉዳይ ነው።

አሞራ ከሰማይ አዞ ደግሞ ከውሃ ውስጥ ሆኖ ነው ነገር ዓለሙን የሚመለከቱ ይላሉ ዓፋሮቹ ሲተርቱ። እይታውንም፣ አድማሱን አረዳዱንም የሚወስነው ከተመልካችነቱ (Vintage Point) ማዕዘን ወይም ገዢ መሬት ነው ማለታቸው መሰለኝ። የአካባቢ ታዛቢዎች መነፀራቸው አካባቢያዊ ነው። ሰፋ ያለውን ሥዕል ይሰጣሉ ብዬ ያሰብኩትን አካባቢያዊ እይታዬን ላስቀድም። በአካባቢያችን የጠላት ተቃዋሚ ካርድ መማዘዙ ርእሰ ጉዳይ ታሪካዊ ዳራነቱ አንጥፈን ለጥቆ ያሁኑ ቃል ኪዳን መስራቾቹ ማለት "አሥመራ ላይ የመሸጉ" የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎችና የኤርትራ ገዢ ፓርቲና መንግሥት መዳረሻ ግቦችን ዳሰሳ እንዘልቃለን።ለትብብሩም ለቃል ኪዳኑም መሠረቱ እሱ ነውና።

የአካባቢያችን መንግሥታት በጥቅል የኤርትራ መንግሥት ደግሞ በተለይ የ 25 ዓመት እድሜው የተቃዋሚ ካርድ መማዘዙና አጠቃቀሙን ከመመልካታችን በፊት የሁለቱ ትብብርና ቃል ኪዳኑ የቆመበትን መሠረት ለመዳሰስ የሁለቱ ተባባሪዎች ከትብብራቸው የሚሹትን መዳረሻ ግብ በመመልከት እንጀምር፣ ነፃ ከወጣ በኋላ የራሱንም ሆነ የሁለቱ ሕዝቦች ትስስር ምንነት የሚወሰነው ነፃ የወጣው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ተብሏልና እሱን ለጊዜው እንለፈው፣

- "አሥመራ ላይ የመሸጉ" ተቃዋሚ ኃይሎች የኢትዮጵያን ሕዝብ ነፃነት ይሻሉ።
- የኤርትራ መንግሥትና ገዢ ፓርቲው ሻዕቢያ የኤርትራ ነፃ ሃገራዊ ሕልውና በተደላደሉና አስተማማኝ መሠረቶች ላይ ማረጋገጥ ይሻሉ።
- የኤርትራን ነፃ ሕልውና ማረጋገጫ እንዲያገኝ የኢትዮጵያ የአንድነት ኃይሎች ይሁንታ እንዲታከልበት ይሻሉ።
- የሃገር አድን ጥምረት ሆነ ሌሎች "አሥመራን ምሽግ ያደረጉ" ኢትዮጵያውያን ድርጅቶች መዳረሻ ዓላማቸው ያደረጉትን የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነትና የኤርትራ መንግሥትና ገዢ ፓርቲው ሻዕቢያ ከእነሱ የሚጠብቀውን የኤርትራን ነፃ ሕልውና ማረጋገጫ ሊያረጋግጡላቸው ይችላሉን? የኤርትራ መንግሥት ደግሞ እነሱን በማስፈራሪያነት ብቻ ተጠቅሞ መደራደሪያ እንዳያርጋቸው አስተማማኝ ማረጋገጫ ሊሰጣቸው ይችላልን?
- የሁለቱ መዳረሻ ግቦቻቸውን ሚዛናዊ በሆነ መልክ አቀናጅቶ ለሁለቱም ቃል ኪዳን ሻሪኮች የጋራ ዓላማ የሚበጅ ዘላቂ ፀረ ወያኔ ኢሕአዴግ ትብብር በመፍጠር ወያኔ ኢሕአዴግን ማስወገድ ይችላሉን?

የሁለቱ የትብብር ዓላማ ሊታረቅ የማይችል ቅራኔ ባይሆንም ቅሉ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ሁለቱን ማጣመሩ ነው ከባዱ ሥራ ። ያንድ መንግሥትና የአንድ ነፃ አውጪ ጥምረት ፍላጎቶችን አጣጥሞ ማራመዱ ከችግር ነፃ አይደለም። ሊሆንም አይችልም።

ጀርመኖች die Kunst besteht darin ወይም ኪነጥበቡ እሱ ነው ይላሉ። አስቸጋሪውና አሳሳቢውም እሱ ነው ለማለት ይመስለኛል። የፖለቲካ አመራሩ ብቃት ጥበብ አንዱ መመዘኛም ይህንን በጥበብ ማለፍን ይጨምራል ማለታቸው ነው። የሸሪኮቹ እኩል አለመሆን ራሱን የቻለ አንድ ተግዳሮት ነው። ባስተናጋጁ መንግሥት በኩል ተስተናጋጁን ማስተናገዱ ራሱን የቻለ የሃገር የድህንነት ዶሴ አካል ሆኖ መቆጠሩ ሌላኛው አበሳ ነው። እነዚህን ሦስት ታሳቢዎችና ተግዳሮቶችን ያዙልኝ።

**የተቃዋሚ ካርድ መማዘዙ ፖሊሲ**

ለአካባቢ ሃገራት የተቃዋሚ ካርድ መማዘዙ ጨወታ አዲስ ነገር አይደለም። ያንዱን ጎሮቤት ሃገር ተቃዋሚ ማስተናገድ፣ ማደራጀት፣ ማስታጠቅና ማሰማራት የተለመደ አሥራር ነው ማለቱ ይቀላል። ለነባር መንግሥታትም ሆነ ለአዲስቷ ሃገር ኤርትራ የአጎራባች ሃገራት ግንኙነት አስመልክተው የነደፉት የውጭ ፖሊሲያቸው አንዱ ማሞርኮሻ ነው ቢባል ምንም ማጋነን የለበትም። የኤርትራ መንግሥት በአካባቢ መንግሥታት ላይ የራሳቸው ተቃዋሚ በማደራጀት ተጽእኖ የማሳደር ፖሊሲ አካል ነው። ማስፈራሪያ ካርድም ነው። የሱዳን፣ የሶማሊያ፣ የጅቡቲና የኢትዮጵያ ተቃዋሚን ያደራጃል። ይህ ምስጢር አይደለም። ባንድ ወቅት የየመንም ተቃዋሚ ሲያደራጅ አልፎ ተርፎ በካቢላ ለሚመራው የኮንጎ ነፃ አውጪ ሠራዊት ጎን የሚሰለፍ ኃይል የላከበት ሁኔታ እንደ ነበረ ይነገራል። ይህንን የሚመሰክሩት  በውጭ ሃገር የሚኖሩ በዘመቻው የተሳተፉ ኤርትራውያን ወታደሮች የነበሩ ወጣቶች ናቸው። እነዚህ ተግባራት እንደ አንድ የሃገር ደህንነት ጥበቃ ጉዳይ (ዶሴ) አካል ሆነው ነው የሚታዩት። የኤርትራ ደህንነት መሥሪያ ቤት ሚና ከዚህ በፊት የተበጃጁትን ትብብሮች በማለያየትም ሆነ በማገጣጠም የራሱ የማይናቅ ሚና ነበረው። ዛሬም አለው።

የጫወታው ሕግ ዋናው መሠረቱ ተግባርና አፀፋ መልስ ነው። የእኔን ተቃዋሚዎች ብትረዳ እኔም በአፀፋውና በተራዬ ያንተን አደራጅቼ፣ አስታጥቄ እለቅብሃለሁ ዓይነት ማስጠንቀቂያ ይጀምርና እስከ ከተቃዋሚ ኃይል ጎን ተሰልፎ አብሮ ማጥቃት ደረጃ ይደርሳል። አንዳንድ ጊዜ ማስፈራሪያው የምር ይሆንና በሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት ከእነጭራሹ እስከ ማስወገድ ድረስ ዓላማ ይዘልቃል። አፕሪል 1979 የዚያን ጊዜ የታንዛኒያ ፕረዝዳንት የነበሩት ጁሌየስ ኒሬረ የቀድሞ የዩጋንዳ ፕረዝዳንት የነበሩትን ሚልቶን ኦቦቴን በራሳቸው ሠራዊትና ታንኮች አጅበው ፊልድ ማርሻል አልሃጂ ኢዲ አሚን ዳዳን አስወግዶ በካምፓላ እንደ ገና ለመንግሥት ሥልጣን ያበቁበትን አብነት መጥቀስ ይቻላል። ይህ ግን በየጊዜው የምንመለከተው ክስተት አይደለም። የተቀዋሚ ካርድ አብዛኛውን ጊዜ ከማስፈራሪያ ካርድነት አያልፍም።

የሱዳኑ ኡማ ፓርቲ መሪ ሳዲቅ አል ማህዲ፣ የሶማሊያው አልሻባብ መስራችና መንፈሳዊ መሪ ሓሰን ዳሂር ዋዒስ፣ ሙባራክ ሙሳ ሙባራክ፣ የሱዳኑ የረሻይዳ አንበሶች መሪ ፣ የቤጃ ኮንጎረስ መሪ ሙሣ አህመድ ሁሉም የኤርትራ መንግሥት እንግዶች ነበሩ ባንድ ወቅት። ከሁሉ በላይ በአሜሪካም ጭምር ለወደፊቱ የሱዳን መሪነት ሲታጭ የነበሩት ጄነራል ዓብዱልአዚዝ ካሊድንም ለዚህ ኃላፊነት ሲያዘጋጁቸው የነበሩት አሥመራ ላይ ሆነው ነው። እንዲያውም የሱዳን እጣ ፋንታ ወሳኝ ቁም ነገሮች ጉባኤ (አል–ቀዳያ አልመሲርያ) የተሰኘው የሱዳን ተቃዋሚዎች ኮንግረስ በ 1995 የተደረገውም በአሥመራ ላይ ነው። ዛሬ ሁሉም ማለት ይችላል ወደ ሃገራቸው በመጡበት እግር ጠቅልለው ተመልሰዋል። ገሚሱ ከመንግሥት ጋር ታርቆ ሹመት፣ ሽልማት ተቀብሎ ነው። ገሚሱ በሃገሩ አሁንም ሰላማዊ ተቃውሞ ፖለቲካውን በማጧጧፍ ላይ ይገኛል። 2012 ጀምሮ ሓሰን ዳሂር ዋዒስ በሶማሊያ እስር ቤት እንደሚገኙ ይታመናል።

ምንም እንኳን በቅርቡ በተደረጉ ሹም ሽሮች ከሥራ ምድቦቻቸው ቢዘዋወሩም ቅሉ የረሻይዳ አንቦሶች  እና የቤጃ ኮንግረስ መሪዎች በቀይ ባሕር ክፍለ ሃገር ከፍተኛ ቦታ ተሰጥቷቸው ነበር። ስለዚህ የሱዳን አል በሺር መንግሥት ከሥልጣን ባይወገድም የፕረዝዳንት ኢሳያስ መንግሥት የሱዳንን ታቃዋሚ ካርድ በመጠኑም ቢሆን የተወሰነ ተጽእኖ ለማሳደር ተጠቅሞበታል ማለቱ ያስኬዳል። ለዚህ ስኬትና የሰመረ ውጤት ግን በዋናነት ሊጠቀስ የሚገባው የሱዳን መንግሥት ለድርድር የሚያሳየው በጎ

ፈቃጅነትና ፍላጎትን ነው ማለት ይቻላል። በአዲስ አበባና በአሥመራ እንደ ከተሙት ሁለቱ የሓበሻ መንግሥታት በጠላቶቼ መቃብር ካልፎከርኩ ብሔራዊ መግባባትም ሆነ እርቅ አይነካካንም አይሉም ሱዳኖቹ፣ መንግሥትንም ሆነ ተቃዋሚውን የሚያስመሰግናቸው እሴት ነው።

በነገራችን ላይ ፣ የኤርትራ መንግሥት ብቻ አይደለም በአካባቢ መንግሥታት ላይ የራሳቸው ተቃዋሚ በማደራጀት የራሱ ተጽእኖ የማሳደር ፍላጎትና ፖሊሲ የሚነድፈው። የቀድሞ ሶማሊያም፣ ሱዳንም ኢትዮጵያም ተመሳሳይ እንደ አንድ የሃገር ደህንነት ጉዳይ (ዶሴ) አካል ሆኖ የሚታየው ፖሊሲ ነበራቸው። አሏቸውም። የተቃዋሚዎች ካርድ መጠቀም የብሔራዊ ደህንነት ጉዳይ እስከሆነ ድረስ የሃገር የሕልውና የመጠበቅ ጉዳይም ጭምር  ነው። በ1998 አጋማሽ ላይ የሁለቱ ገዥ ድርጅቶች ትብብርና ቃል ኪዳን ከተፋለሰ በኋላ በርካታ ኢትዮጵያውያን ወደ አሥመራን ጎራ ብለዋል። ገሚሱ በሄደበት እግሩ ተመለሷል። አንድ ነገር ግን መባል አለበት። መባል ብቻ ሳይሆን መሰመር ይኖርበታል። ኢትዮጵያ ለኤርትራ፣ ሱዳንም፣ ሶማሊያም ጀቡቲም አይደለችም። ለፖለቲካው ፍጆታ የሚባለው ከኢትዮጵያ ጋር ያለን ትስስር ልክ ከሌሎቹ አጎራባች ሃገራት ጋር ያለን ትስስርና ባይነ መንግሥታዊ ግንኙነት ነው መባሉ እንደ ተጠበቀ ሆኖ። ኢትዮጵያ ለኤርትራ ታላቋ ጎረቤትና የቀድሞ "ቅኝ ገዢ " ብቻም አይደለችም። ሁለቱ ገዢ ፓርቲዎች ወዳጅነትና ጥል፣ የሁለት ሕዝቦች ያለፈውን የጋራ ታሪክና የወድፊቱ ጎን ለጎን በይነ መንግሥታዊ ጉርብትናም ሆነ ጥምረታዊ ንድፎች የሁለቱን መንግሥታትም ሆነ ሕዝቦች ትስስርም ሆነ ትብብር ልዩ ያደርገዋል፣ ያለ ጥርጥር። በመረብ ወንዝ –ሸገር ያሉ ትግርኛ ተናጋሪዎች የኤትኒክ ማንነት ተጋሪዮሽነት ጉዳይ በዋናነት ይጠቀሳል። እነሱ እንደ ፖለቲካው ሁኔታው  ቢቀበሉም ቢካካዱም። በሁለቱ ሕዝቦች ቁርኝት ምክንያት ደግሞ ለሁለቱ መንግሥታትና ገዢ ፓርቲዎች አንዱ የሌላውን ተቃዋሚ መጠቀሙ ልዩ እንደምታ የሚሰጠው ከዚህ ልዩ ትስስር በመነሳት ነው። ከሱዳኑ፣ ከጀቡቲ፣ ከሶማሊያው ይለየዋል። የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ካርድ መምዘዝና አጠቃቀሙ ከላይ ካየነው የአካባቢ ሃገራት አጠቃቀምና አተገባበር በይዘቱም ሆነ በዓይነቱም ይለያል። ለኢትዮጵያ የኤርትራ ተቃዋሚ ካርድ አጠቃቀሙም እንዲሁ። ለዚህ ከላይ ከተመለከትናቸው እሳቤዎች በተጨማሪ በቂ የዳራ ምክንያቶችም መደርደር ይቻላል።

የተቃዋሚ ካርድ መዘዛው የሃገር ደህንነትና ሕልውና ነክ በመሆኑ ምስጥር ይበዘዋል። እንዲያውም ዓዋቴ የተባለው ታዋቂው የኤርትራ ድረ –ገጽ የሁለቱ ሓበሻ መንግሥታት ተቃዋሚን ማደራጀት፣ ማሰልጠን፣ ማስታጠቅና ማሰማራት የደህንነት መሥሪያ ቤቶች መካከል የሚደረግ ፍልሚያ (The Ethiopian-Eritrean Intelligence War) አድርጎታል። http://awate.com/the-ethiopian-eritrean-intelligence-war/። ምስጥር ደግሞ ከገበያ የጠፋ ብርቂዬ እቃ በሆነበት የፌስቡክ፣ የቱዊተር፣ ዘመነ ዲጂታል ሊሸፋፈን አይችልም። በደርግና በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ያልነበሩ ዘመናዊ ፈጥኖ አድራሽ ዲጂታል የማሕበራዊ መገናኛ ዘዴዎች ሁሉም ሽፍንፍኑን፣ ግልብልብ ግልጥልጥ ባደረጉበት ዘመን ነውና ያለነው ። ያውም በሙብረቅ ፍጥነት። ሰሞኑን በሞላ አስገዶም ጉዳይ የተመለከትነውም ይህንኑ እውነታ ነው። የሞላን ፍርጠጣ ልብ አንጠልጣይና ገደል ተቆንጣጭ thriller ፊልም ያስመሰለው የእነዚህ ማሕበራዊ ሚዲያዎች አቀራረብም ጭምር ነው።

በኤርትራ ብቻ ሳይሆን ከላይ በተጠቀሱት ሃገሮች ሁሉ የተቃዋሚዎች ካርድ ጉዳዩ የብሔራዊ የደንህነት ጉዳይ ሆኖ ስለምታይ በአካባቢ ሃገራት ልሙድ አሰራር ነው። አሁንም በሱዳንም፣ በሶማሊያም በኢትዮጵያም ተዘውታሪ አካሄድ ነበር ብለናል። በዚያድ በሬ (1969 - 1991) ሶማሊያም አሠራሩ ከዚህ የተለየ አልነበረም። የኤርትራና የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች ዋና አገናኝ መኮንኖች ተብለው የሚታወቁት የፕረዝዳንት ዚያድ በሬ አማች (የልጅ ባል) ኮለኔል ሱሌማን ዳፍሌና የውጭ ሃገሩን የሚያስተባብሩት አምባሳደር ዓብዱ ሓበሺ በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ። ዛሬ ኮለኔል ሱሌይማን ዳፍሌ የቤልጂም ስደተኛ ሲሆኑ አምባሳደር ዓብዱ ሓባሺ ደግሞ የሚኖሶታ ስደተኛ ናቸው። ዓለም ተቀያይራ ዳፍሌ በ1990ዎቹ አጋማሽ ላይ በስደተኛነት ወደ ኤርትራ ጎራ ባሉበት ወቅት ፕረዝዳንት ኢሳያስ ለቆየው ትብብሩና ለሞቃዲሾው መልካም መስተንግዶው ውለታ የወደቦቹ ባልሥልጣን ሥራ አስኪያጅ የነበሩት ኮማንደር ዘለቀ ቦጋለ በዓሰብ ወደብ ከሠሯቸው በባሕር ጠረፍ ከተንጣለሉ ቪላዎቹ አንዱ ውስጥ እንዲስተናገዱ አድርገዋል።

በሱዳን ደህንነት መሥሪያ ቤት በኩል ሦስት ጀኔራሎችስማቸው ከወያኔና ከሻዕቢያ አስተናጋጅነትና ምስጥር ጣባቂነት ሲጠቀስ ይኖራል። ሜጀር ጄነራል ፋቲሕ አል አርዋ፣ ዑስማን ሳይድና ሙስጣፋ አህመድ ዳቢ። የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማ አልፋቲሕ ዓርዋ የተባለው የሱዳኑ ጄኔራልና ፓይሎት በመቀሌው 39ኛ የወያኔ ድርጅታዊ ጉባኤ ላይ ፕሪዝዳንታቸው ዑመር ሓሰን አል በሺር በተገኙበት የዘከዘኩት ምስጥረ ምስጥራት ጉድ ያሰኘው እስከ እዚያ ቀን ድረስ አልተሰምቶም የነበሩትን ጭምር ይፋ ስላደረጉ ነው። ቀደም ብሎ በደርግ ዘመን የሱዳን ሚሊተሪ አታሼ ሆኖ አዲስ አበባ በሠሩበት ጊዜ ሌሊት በቢስኪሌት እየተዘዋወሩ ከወያኔ የውስጥ አርበኖች ጋር እንደሚገናኙ ጭምር ነው ጀኔራሉ የነገሩን። A Sudanese Offcial Reveals TPLF Secrets (https://www.youtube.com/watch?v=yfeBMv885pk) ዩቱዩብ መመልከት ይቻላል።

በኢትዮጵያም ጉዳዩ ከዚህ የተለየ አልነበረም። አሁንም አይደለምም። ዛሬ ወያኔ ባመዛኙ የቀድሞ ኢ.ሌ.አፍ (ጀብሃ) ጋር ቁርኝት የነበራቸውን የኤርትራ ምዕራባዊ ቆላ ተወላጆች በተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች በማስተናገድና በማስተባበር የመረብ – ሸገር ትግርኛ ተናጋሪ ዘመዶቹን እነ ዓብዳላን ነው የምንለቅባችህ እያለ በማስፈራረት ልክ ለማስገባት የሚሞክሩበት አተገባበር ልብ እንላለን። አሁንም የሰንዓ መድረክም (Forum ) ተብሎ የሚታወቀው አካባቢያዊ ማስተባበሪያ የኤርትራ ተቃዋሚዎች ጉዳይ ይከታተላል ይባል እንጂ ኃላፊነቱን ከላይ የሚያስተባብሩት የደህንነት ጀኔራሎች ናቸው። ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ጀምሮ እምብዛም አልተለወጠም። ትናንት በደርግ ዘመን የኮሌነል ተሰፋዬ ወለደ ሥላሴ ልጆች ዛሬ ደግሞ የጀኔራል መስፍን አማረ፣ ጌታቸው አሰፋና የኢሳያስ ወልደ ጊዮርጊስ ጓሮ አትክልት ነው፣ ተቃዋሚዎችን ማስተናበሩ። ኢትዮጵያ የደቡብ ሱዳንን አመጽ ማገዝና ማስተባበር የጀመረቸው ገና በ1960ዎቹ ጅማሮ ላይ ነው። የኑዌሩ ተወላጅ ቲዋት ፖል ቻይ የጋምቤላ የፓርቲ መሪነቱን የተቆናጠጠው በደህንነት መሥሪያ ቤት ቅርንጫፍ አስተባባርነቱ ነው። በዛርዩቷ ኤርትራ ጀኔራል ተክለ መንጁስ፣ ኮሌኔል ፍጽም(ሌነን)፣ ሸላቃ ዳዊት ስሞች በበርካታ ኢትዮጵያውን ዘንድ ለመታወቅ የበቃው የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች ዶሴ ባለ አደራነታቸው ነው። የጎረቤት ሃገር ተቃዋሚ ካርድ መማዘዙን ታሪክ በመጠኑ ተመልክተናል ። የሃገራዊ ደህንነት ጉዳይ መሆኑን ልብ ብለናል። የስጋት ምንጭ ፣ ከሃገር ሕልውና ጋር በጥብቅ የመተሳሰሩን ቁርኝት በእሳቤ እንዲወሰድ ነው አጽናኦት የተሰጠው።

**የአማራ ልሂቃንና የኤርትራ መንግሥትነት መረጋገጥ**

“ሻዕቢያ ኢትዮጵያ እስካልፈራረሰች ድረስ ኤርትራ ሙሉ ነፃነቷን ገና አላገኘችም ብሎ የሚያስብ ድርጅት ነው“ የሚለውን አባባል ሙሉ በሙሉ እንዳለ መቀበሉ ያስቸግረኛል። የኢትዮጵያ አንድነት ሃይሎች እስልተቀበሉት ድረስ የኤርትራ ነፃነት ዋስተና አይኖረውም የሚል ስጋት ሻዕቢያን እንደሚያንገላታ መቀበሉን ግን በፍፁም አያስቸግረኝም። ስጋቱ የኤርትራ ብሔረተኛ ኃይልን ከእንቅልፉ ያባንናል ማለቱ ይበልጥ ሁኔታውን ይገልፀዋል።
ወያኔና ሻዕቢያ አሁንም አልተጣሉም ክርክር ግን ውሃ አይቋጥርም። ነገ ተነጋግረው ሊታረቁ ይችላሉ መባሉ ጋር ግን ጠብ የለኝም። ይህ እውነት ከግንቦት ሰባት መሪዎች አንዱ በቅርቡ በአሜሪካ ባደረጉት ንግግር አስምሮበታል። እንዲያውም ግንቦት ሰባት የሚጣደፈውም ለዚሁ ነው ብሎ እንቅጩን ነግሮናል። ይህ እምብዛም የሚያከራክረን ነጥብ አይደለም። ወያኔና ሻዕቢያ በፀረ ደርግ ቃል ኪዳናቸው የሁለቱን መዳረሻ ግብ ማሳካትን ቻሉ። የዚህ የተሳካ ትብብር ውጤት የኤርትራን ነፃ ሕልውና ማወጅ እና የወያኔ የምኒሊክ ግቢ ጌታ መሆንን አስቻለ። የሁለቱም ተባባሪዎች ዓላማ ግቡን መታ ቢባል ያስኬዳል። ከሰባት ዓመት ትብብር በኋላ ሁለቱ በጋራ ያሳኩትን ዓላማ እንዳልነበረ ለማድረግ ባሁኑ ጊዜ አንዱ የሌላውን ተቃዋሚ አሰልጥኖ እያሰማራበት ይገኛል። ይህ የኮኒስፒራሲ (የሤራ) ትዮሪ ጥዶሽ አይደለም። ሃገራት የሚወዳጁበት የጋራ ዓላማ ሲገኝ ይፋቀራሉ ሲፋለሱም አንዱ ሌላውን ልክ ለማስገባትም ሆነ ከእነአካቴው ለማስወገድ ይውተረተራሉ። በሚያገናኛቸው የጋራ ዓላማ ዙሪያ ይተባበራሉ እንጂ አይቆራረቡም። መዘንጋት የሌለበት አንዱ ዋነኛው ነጥብ ይህው ነው። በትግራይ ነፃ አውጪዎች እርዳታ፣ አጋርነትና አማኻኝነት የተረጋገጠው ነፃነት የኢትዮጵያ አንድነት ኃይሎች ይሁንታም እንዲታከልበት ይፈልጋል ሻዕቢያ። ካልታከለበት ግን የኤርትራ ነፃነትና መንግሥትነት ማረጋገጫ እንደሌለው ይቆጠራል። የሻዕቢያ ዓላማም ግብ መታ ማለት

የሚቻለው ይህንን ተቀባይነት ሲያረጋግጥ ነው።

በርካታ የኢትዮጵያ አንድነት ኃይሎች ግን የኤርትራ ነፃ መንግሥትነት አልተዋጠላቸውም። የእዚህ ብሔረተኛ ኃይል በአመዛኙ መሠረቱን የገነባው በአማራ ልሂቃን ዙሪያ ምሕዋር ይሽከረከራል መባሉም እምብዛም ማጋነን የለበትም። አንዳንድ ጊዜ ሁለቱ አንድና አንድ ይሆናሉ። ይህ ያንድነት ሃይሎች የተሰኘው ስያሜ የአማራ ኤሊቶች ሌላኛው ማሽሞንሞኛ መጠሪያ ነው ወይ የሚል ጥያቄ የሚያስከትለውም ለዚህ ነው። ማስከተሉ እምብዛም ስሕተት የለበትም። ለዚህም ይመስለኛል በቅርቡ ሔኖክ የሺጥላና ወልደሩፋኤል አሰፋ የተባሉት ጸሓፊዎች የአማራ ኤሊት በስም ጠርተው ከኤርትራ ጉዳይ ጋር ያጣመሩት። እንዲያውም ወጣቱ ገጣሚ ሄኖክ የሺጥላ ***የአማራ ኤሊቶች ትግልና የኤርትራ ጉዳዩ*** በተሰኘው አርቲክል የአማራ ኤሊቶች እነሱ ያልተሳካላቸውን ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋና የእሳቸው ቡድን ስለተሳካለት በቅናት እንደተብሰከሰኩ አስመሰሎ ነው ጉዳዩን ያሳረገው። ከዚያ ቀደም ብሎ ወልደሩፋል አሰፋ የተባለ ወጣትም ***የአማራ ኤሊቶችና የኤርትራ ጉዳይ*** የሚል መጣጥፍ አስነብቦን ነበር። ሁለቱ መጣጥፎች ግን አንድ ጥያቄ ይጭሩብኛል። ለምን የአማራ ኤሊቶች በተለይ ተመረጡ? ይሳካልኝ እንደሆነ አላውቅም እንጂ እኔም አማራ ኤሊት የተባለው የኢትዮጵያ ብሔረተኛ (አንድነት) ኃይል ወደ ተሰኘው በማስፋት የውይይቱን አድማስ ሰፋ ለማድረግ እሞክራለሁ።

ዛሬ ኤርትራ የተባበሩት መንግሥታት አባልና እውቅና የተጎናፀፈች ራሷን የቻለች ሃገር ብትሆንም ቅሉ ከ25 ዓመታት በኋላ ከአጎራባቿ ኢትዮጵያ ጋር ጎን ለጎን በይነ መንግሥታዊ ጉርብትናም ሆነ አዘቦታዊ በይነ መንግሥታዊ ግንኙነት መመሥረት አልቻለችም። ይህ ለኤርትራ መንግሥት ቀላል ተግዳሮት አይደለም። በመሪዎቿ እይታ ያለ ኢትዮጵያዊ አንድነት ኃይሎች ይሁንታ ሙሉ ነፃነቷ እንደማይደላደል ከመስጋት ነፃ ወጥተው አያውቁም። ከኢትዮጵያ ጋር ማለፊያ በይነ መንግሥታት ግንኙነት ሊኖራት አይችልም የሚል ስጋት የኤርትራ መሪዎችና ገዢው ፓርቲውን ሁሉ ጊዜ ያባንናል። ይህን ለማወቅ የግድ የጂዮ –እስተራተጂ ባለራዕይ መሆን የሚያስፈልግ አልመሰለኝም። የኤርትራ ነፃነት በወያኔ እርዳታ ቢጠናቀቅም ያለ አማራ ኤሊቶች ቡራኬ ዋስትና የለውም ባይ አመለካከት ፕረዝዳንት ኢሳያስንና አመራሩን እንቅልፍ ይነሳቸዋል። ይህም የአማራ ኤሊቶች ወግ ጠራቂ ኩፈሳ አይደለም ። የኤርትራ ተቃዋሚዎቹ የኤርትራ ነፃነት የማይዋጥላቸው የቅንጅት ቀድሞ አባላትን በአሥመራ እያሞላቀቅክ ነው ብለው ፕረዝዳንት ኢሳያስን ይወቅሱታል። የቅንጅት አባላት የሚሉት የኢትዮጵያ አንድነት ኃይሎች ወይም አማራ ኤሊቶችን ነው። አማራ እንኳን ኤሊቶች ሊኖሩት ቀርቶ እንደ አንድ ስብስብ የመኖሩ ክርክር ገና መቼ በቅጡ ተቋጨና የሚለው እልባት ያልተበጀለት እስጣ አገባ ውስጥ እንደሚዘፍቀን አልዘነጋሁትም። ይህንን ታአቅቦ እንዳለ ተቀብለን ነው የኢትዮጵያ አንድነት ኃይሎች ተብለው በሚደራጁት ያንድነት ኃይሎች በስተኋላ ሁል ጊዜ የአማራ ኤሊቶች ፈልጉ የሚለው አባባል "የአክራሪ ተገንጣይ ብሔረተኛ" ወገኖች ብቻ አይደለም በማለት ነው ስምምነቴን የማክለው። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ የኤርትራ ገዢ ፓርቲና መንግሥት እንዲሁም የኤርትራ ተቃዋሚ ኃይሎች ጭምር ከዚህ የተለየ አመለካከት ያላቸው አይመስለኝም።

ፕሮፌሰር መስፍን ዛሬም አማራ የሚባል ነገድ እንደ ማህበረ ፖለቲካዊ ስብስብ የለም እያሉን ነው። ከፍ ቢል እንደ ኢትጵያዊ ዝቅ ሲል ደግሞ እንደ ያንድ አካባቢ ልጅነት ማለት እንደ ጎንደሬ፣ጎጃሜ፣ ሸዌ፣ ወሎዬ ይመለከት ይሆናል እንጂ ራሱን እንደ አንድ ብሄረሰብ ተመልክቶ አያውቅም ነው መከራከሪያ ነጥባቸው። የዛሬ 25 ዓመት ገደማ ጀምሮ አማራ እንደ ማኛውም ብሔር፣ ብሔረሰብ መብቱን ሲነፈግ አልፎ ተርፎ የጥቃት ሰለባ ሲሆን በግድ እንደ ሌሎቹ ማንነቱን ፈልጎ ያገኛል፣ አልፎ ተርፎ ብትሩ ሲበረታበትም ለመመከት የግዱን በአማራነት ይደራጃል በሚለው ፈሊጥ (ስተራተጂ?) የዛሬ ገዢዎች ተፈታተኑት። በነገዱ እንዲደራጅም ገፋፉት። በተወሰነ ደረጃም ተሳካላቸው። በኋላ ወደ መላ ኢትዮጵያ ቢቀይርም ቅሉ መላ አማራ ድርጀትም አንድ አብነት ነው። ምንም እንኳን በኋላ ላይ ጸሓፊው ራሱ ይቅርታ የጠየቀበት ድርጊት ቢሆንም ቅሉ የአቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ***የአማራ ዲሞክራሲያዊ ብሔረተኛነት*** መጽሓፍም ሌላኛው ተጠቃሽ ዋቢነት ነበር። በሌላ አነጋገር እንደ ማኛውም ስብስብ ብሔረሰብነትህን ተቀብለህ ተደራጅ ባይ ወያኔና ሻዕቢያ አልደራጅም ባይ አማራ ኤሊት መካከል የተካሄደ

ግብግብ ነበረ ማለቱ ምንም ማጋነን የለበትም። ይህ ግብግብ ሌላ አድማስ ነበረው። የዚህ በነገድህ ተደራጅ ወከባ የኤርትራን ነፃ መንግሥትነት በግዱ ትቀበላታለህ ትርጉምም ነበረው። ነፃነቷን የተቀዳጀችው ኤርትራ ነፃነትና መንግሥትነት በግድህ ትጋታለህ የሚለው ከአማራ ኤሊቶች ጋር የተያያዘው ትዩዩ ግብግብ መልክ ነበረው። ወደ አሥመራ ይቅርታ ጥያቃ የተጓዘው ልዑክም ተልእኮው ከዚህ ግብግብ ተለይቶ ሊታይ አይችልም። የወያኔና ሻዕቢያ ወዳጅነት ዘመን (1991 - 1998) ሁለቱ ግብግቦች አንድም ሁለትም ነበሩ። አራማጆቹ በአሥመራና በአዲስ አበባ ሥልጣን የተቆናጠጡ ገዢ ፓርቶዎችና ሻሪኮች ነበሩ። ምክንያቱም ግልፅ ነው። ያኔ ሁለቱ የተለያየ እስተራተጂካዊ ግብና መዳረሻ ዓላማ አልነበራቸውምና። ገዢ ፓርቲዎቹ አንድም ሁለትም ነበሩና። ሁለቱ አማራን የሚፎካከሩት አንደ ትግራይ –ትግሪኝ ብሔረተኛነት ካባ ደርበው ነው።

ዋለልኝ መኮነን የዛሬ 50 ዓመት ገደማ በስመ ጥሪው ***የብሔረሰቦች ጉዳይ*** መጣጥፉ በኢትዮጵያ በተዘረጋው ፊውዱዋላዊ ሥርዓት አማራ ዋና ጨቋኝ ሲሆን ትግራዊው የጭቆናው ተባባሪና በሥልጣኑ አናሳ ድርሻ ባለቤት ሽሪክ (Junior Partner) አድርጎ ነው ያስቀመጠው። በመሓሉ ብዙ ውኃ በድልድዩ ሥር ፈሷልም፣ አልፏልም። ዛሬ ትግራዊው አናሳም አይደለም። በቁጥር ማለቴ አይደለም። ንዕስ የሥልጣን ሽሪክም አይባልም። ባለ ጊዜና "ገባሪ ሓዳጊዎቹ" የትግራይ የሥልጣን ኤሊቶች ናቸውና። እነሱ በሃገሪቷ በዘረጉት ሥርዓት እነሱ የሥልጣን እርፍ እየዘወሩ ሌሎች ኤሊቶች በሽርክናም ሆነ በአጋሪነት ስም አናሳ ሚና እየተጫወቱ ናቸው።*ያ ቀርቶ ሌላ ዘፈን* ................ይባል የለ!

በመደምደሚያ አንድ ጥያቄ ለግንቦት ሳባት አርበኞች መሪዎች ሊወርውር። እስካሁን በተደረጉ 30 ዓመታት በፈጀው የኤርትራ የነፃነት ውጊያም ሆነ 17 ዓመታት በወሰደው የደርግ ወያኔ ጦርነት ማን፣ ምን እንደሚረዳቸው በጣም በጣም የሚጠበቅ ምስጥር ነበር። እነዚህ ድርጅቶች ሱዳንም ሆነች ሌሎች ዓረብ ሃገራት የሚያደርጉላቸው እርዳታ ከጃንሆይ እና ከደርግ መንግሥታት እንጂ ከራሳቸው ከድርጅቶችም ሆኑ ከመሪዎቹ አንደበት ስምተን አናውቅም ነበር። የኢትዮጵያ መንግሥት ግጭቱ የሁለት መንግሥታት ቀጣይ ግብግብ እንደመስልለት መፈለጉን መረዳት አይገደም። ምክንያቱ እምብዛም አያመራመርምና። ለምን አርበኞች ግንቦት ሰባት መሪዎች ግብግቡን ይህንን መልክ እንዲሰጠው የሚሹበት ምክንያት ግን እስካሁን ሊገባኝ አልቻለም። "ኤርትራ የመሸጉ" የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች እስከተባሉ ድረስ ጦርነቱ ከሁለት መንግሥታትና ገዢ ፓርቲዎች ጋር መቆራኘቱና ይህንንም መልክ መላበሱ አይታየንም?

ሌላ ነጥብ ልጨምር መሰለኝ። ሞላ አስገዶም የሚያውቀው ነገር የለውም፣ ኮብለላው በሃገር አድን ጥምረት ላይ ምንም ጉዳት አያደርስም ፣እንኳን በጊዜ ኮበለለ፣ ከህደቱ እንዲያውም Blessing in disguise (ከአበሳ ቱሩፋት አፈሳ?) ወይም የጥራት ሂደት ነው መባሉ ለአካባቢ ታዛቢዎች ሊዋጥ የማይችል አጉል ራስን ማፅናናት ነው። ጉዳቱ ከልኩ እንዳያልፉ ማጠር (damage limitation) የተሠራውን ስህተት ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስ መከላከል ላይ መጠመዱና ሞላ ላነሳቸው ጥያቄዎች መለስ መስጠቱ የፈጀው ጊዜ እንኳን በተግባራዊ የትግል እንቅስቃሴ ኪሣራ እየተደረገ እንደሆነ ምንም አያጠያይቅም። በተቃዋሚዎቹ ጎራ አሁንም ከሁሉ የላቀው ቀሪው የዴምሕት ኃይል ነው። በሰው ኃይልም በትጥቅም። አሁንም ከሻዕቢያ ጋር ያለው የጠበቀ ቁርኝት እንዳለ ነው። አሁንም አመራሩን የተቆጣጠሩት መሪዎች ከሞላ አስገዶም በአቅም የሚልቁ አይመስሉም፣ በእኔ እይታ። *ሓትሰንብዱ* ብሎናል አዲሱ የዴምሕት መሪ መኮነን ተስፋዬ። አትደንግጡ መሆኑን ነው በትግሪኛው። ባያስደነግጥም ያሳስባል። ከሞላ ኮብለላ በኋላ የኤርትራ የደህንነት ሃይሎች ቁጥጥርም ጠበቅ እንደሚል ሳይታለም የተፈታ ነው። በተለይም የአርበኞች ግንቦት ሳባት መሪዎች ስለ ራሳቸው ሲያወሱ "ኤርትራ የመሸጉ" የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይል ብለው እስካስተዋወቁ ድረስ። ሻዕቢያም ወያኔም በሱዳን ይረዳሉ እንጂ ሱዳን ላይ "መሽገናል" የምትል ቃል ካፋቸው በስሕተት አታመልጥም ነበር። ቢመሽጉ እንኳን ሱዳን መሽገናል አይሉም ነበረ። እንዲያውም በትግል ዘመናቸው ሻዕቢያም ሆነ ጀብሃ ያካሄዷቸው የድርጅቶቻቸው ኮንግረሶች ሁሉ ተደረጉ የተባሉት "በነፃ መሬታቸው" ውስጥ ነበር። ይህ "ነፃ መሬት" ራሱ የሱዳን መሬት ካልሆነ ከሱዳን ድንበር ምን ያህል እንደሚርቅ የሚያወቀው ያውቀዋል። በጀብሃ፣ በሻዕቢም ሆነ በወያኔ መዘገበ ቃላት ስለ ሱዳን መመሸግም ሆነ እርዳታ ብሎ የሚነገር ነገር አልነበረም።

አርዱፍ የተባለው የአፋር ተቃዋሚ ድርጅት በደንበሩ አካባቢ የፈረንጅ ዲፕሎማቶችና ቱሪስቶቹን አንድ ጊዜ በኤርትራ አፋር በኩል በራሃይታው ሡልጣን፣ ሡልጣን ዓብዱልቃድር አማኻኝነት ሌላ ጊዜ ደግሞ በኢትዮጵያ ዓፋር ክልል በአካባቢው ባላባት በዳርሣ ዓብዳላ አማኻኝነት መልቀቃቸው የአርዱፍ ታጋዮች በራሳቸው መሬትና ሕዝብ መሓል መመሸጋቸው አንዱ ምስክር ነው ብዬ እገምታለሁ። ይህ ከኤርትራ ደህንነት መሥሪያ ቤት የተወሰነ አንፃራዊ ነፃነት እንደሚያጎናፅፋቸው እሙን ነው። ምክንያቱ ግልፅ ነው። አሥመራ አልመሸገምና። ለሃገር አድን ጥምረት የሠራዊት መዋጮ ተጠይቀው ማቅረብ አለመቻላቸው አስገርሞኛል። ሞላ አስገዶም የተናገረው ሙሉ በሙሉ አይታመንም መባሉ እንደተጠበቀ ሆኖ። በዚያን ወቅት አለቆቻቸው ነን ባዮች ከመንግሥት ጋር ተዋውለው መንግሥት ዘንድ ገብተው ለሹመት ሲባቁ የአርዱፍ ተዋጊዎች እዚያው መሸጋቸውን የሙጥን አሉ ይላል የኢሳት ትንታኑ የፖለትካ ተንታኝ ሲሳይ አጌና የዴምሕትን ሠራዊት ከአላቃቸው ከሞላ ጋር አለመኮብለሉን በቆየው የአርዱፍ ሠራዊት አብነት ሲያስረዳ። አርዱፍ የዴምሕትን ያክል ሠራዊት አይኖረውም ብለን ብንገምት እንኳ ቀላል ግምት የማይሰጠው ኃይል በሜዳው ላይ አሁንም እንዳለው ከአካባቢው ተወላጆች ከሚገኝ መረጃ መረዳት ባይገድም አርዱፍ የሃገር አደን ጥምረት የሠራዊት መዋጮውን ያላሟላበትን በቂ ምክንያት ግን አልታይ አለኝ። ያን ጊዜ በአለቆቻቸው ከደረሰባቸው ክህደት እስከ ዛሬ ባለማጋገም፣ በአላቆች ላይ እምነት ያለ ማሳደር ካሆነ ደግሞ በዲያስፖራ ያሉት የአፋር ድርጅቶች አስተባባሪዎች ልክ እንደ የፕሮፌሰር ብርሃኑና የትግል ጓዶቹ ሜዳ ወርደው ኡጉጉሞን (አርዱፍን) በሚመሩበት ወቅት የትግል ድርሻቸውን ተወጡ ብቻ ሳይሆን መተማመኑንም አሳደሱ ማለት ነው።

የዛሬ ሦስት ወር ገደማ ይመስለኛል የሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት የነፃነት መውጫው መንገድ፣ ታጋዩ፣ ሕዝቡን ጠንካራ ምሽጉ ማድረግ ሲችል ነው የሚል መግለጫ በማውጣት የራሱን አማራጭ የሚመስል ሓሳብ ወርውሮ ነበር። ይበል! የሚያሰኝ ተነሳሽነት ነው። በተለይም የድርጅቱ መሪዎች መፈክሩን በመሬት ላይ ወርደው ተግባራዊ ማድረግ ቢችሉ። ሌላ አማራጭ ካላችሁ አማላክቱን ለሚሉት ወገኖች ሞረሽ የራሱን አማራጭ  አቀረበ ማለት ነውና።

***መደምደሚያ***

የኤርትራ መንግሥትና ገዢ ፓርቲ ፍላጎት ግልፅ ነው። የኤርትራን ነፃነት ማደላደልና ዋስትና ማረጋገጥ ነው። የአርበኞች የግንቦት ሰባት መሪዎች ፍላጎት ኤርትራን ማኮብኮቢያ መሬት አድርገው በመጠቀም የኢትዮጵያን ሕዝብ ከወያኔ ጭቆና ነፃ ማውጣት ነው። ሁለቱን ግቦች ማቀናጀት ይቻላል ብለናል። ይህ ተግባር ምን ያህል በተግዳሮቶች እንደተተበተበ ግን ለማመልከት ሞክሬአለሁ። ሁለቱም ወገኖች አንዱ ሌላኛውን ይሸውደኛል ብሎ መስጋቱ ያልተለመደ ጉዳይ አይደለም። ኢትዮጵያን ነፃ ማውጣት ወይስ የኤርትራን ነፃነት ማደላደልና ዋስትና ማረጋገጥ? የሚለው ጥያቄ  የክርክሮቹና ያለመተማመን ምንጭ ነው ፣ በእኔ እይታ። የሁለቱን ፍላጎት ሚዛናዊ በሆነ መቻቻል ለማረጋገጥ በርእሰ ጉዳዩ ላይም ሚዛናዊ ውይይት እንዲካሄድ የግድ ይላል። በዚህ ውይይት ኢሳት የሚጠበቅበት ሚና አለው ባይ ነኝ። ከኤርትራ መንግሥት ከተቆራኘው ማሕበረ ኮም አባላት ጋር ከሚደረገው ውይይት ይህው በኢትዮጵያውያን መካከል የሚደረግ ውይይት ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል እላለሁ። የኢሳት ሃያልነቱና የትግል ማዕከላዊነቱ የሚረጋገጠው ደግሞ ካንድ ድርጅት ልሳንነት ወደ የሁሉም መድረክነቱ ሲረጋገጥ ብቻ ሳይሆን እነዚህ ዓይነቶች ውይይቶችን ሲመራ ጭምር ነው። የሲሳይንና የኢሳትን ሓዋሪያት አደራ ከባድ የሚያደርገውም ይህንን ጫን ያለውን ትውልዳዊ ኃላፊነት መወጣት ነው።

ልክ በኢትዮጵያን ተቃዋሚዎች መሓል ስለ ትጥቅ ትግሉ መወናጨፊያ መሬት መረጣ ጉዳይ ላይ እንደቀኘነው በተመሳሳይ ሞቅታና ተናዳፊነት "ኢትዮጵያ ላይ የመሸጉ" የኤርትራ መንግሥት ተቃዋሚዎች መሓል የሚካሄድ ውይይትም እንዳለ ስንቶቻችን ነን የምንገነዘበው። ልክ እንደዚሁ በከፍተኛ ደረጃ ይወዛገባሉ፣ ይነታረካሉ፣ ይወራረፋሉ። እርግጥ ውይይቱ ባመዛኙ በትግርኛና በዓረበኛ ስለሚጧጧፍ  ይዘቱን ለመርዳት አጋጣሚውና እድሉ ውስን ነው ለብዙዎቻችን። በሌላ መጣጥፍ በእነሱ መካከል የሚደረገውን እሰጣ አገባ ደግሞ ከዓረብኛውና ከትግርኛው ድረ ገፆች ዘጋግቤ እንደሚመለስ ተስፋ አደርጋለሁ።